22100013

International Baccalaureate
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Thursday 13 May 2010 (afternoon)
Jeudi 13 mai 2010 (après-midi)
Jueves 13 de mayo de 2010 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.





© International Baccalaureate Organization 2010

https://xtremepape.rs/

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጪ)።

**1.**

ከዚያ ሶስት ዙር የምኒሽር ጥይት የታጠቀ ቀድሞ ከተናገረው ሰውዬ በድሜ ላቅ የሚል፣ ፊቱ፡ ኩፋንቻ፣ ልብሱ በጥቁር አፈር የተለወሰ፣ ረጅም ሰውዬ ተነሳና «የተከበራችሁ የሞጣ፣ የብቸና፣ የደብረ ማርቆስና የዳሞት ጀግኖች! እሱ ወንድሜ እንደተናገረው» በማ ለት ንግግሩን ጀመረ። «እሱ» ሲል ባገጩ፡ ቀድሞ ወደተናገረው እያመለከተ «እሱ ወንድሜ እንደተናገረው፣ እንገሱ ድሮም ቢሆን ለጎጃም የሰሩላት የለም ሰሩባት እንጅ። ያለፈውን ትተን አሁን በቅርቡንኩዋ ታውራጃችን መርጠን ስለቀላዱና ስለተጨማሪው የብር ታምሳ ግብር ቅሬታችንን እንዲነግሩልን ወደአገረ ገዡ የላክናቸውን ያገር ሽማግሌዎች ግማሾቹን አስረው፣ ሌሎቹን አቤት ማለት ወንጀል ሆኖ እንደሚያስጠይቅ አስፈራርተው፣ የእንገስ ትዛዝ አይጣስም፣ የእንገስና የግዚሃር ትዛዝ አንድ ነው። የሚል መልስ ተማስጠንቀጫ ጋር ላኩልን» አለና ትንሽ እንደማሰብ ብሎ ንግግሩን ቀጠለ።

«ድሮም ቢሆን እንገሱ ራሳቸው ተባለሙዋሎቻቸው ጋር አገራቸውንና ህዝባቸውን ለጥሊያን አጋፍጠው ሲፈረጥጡ፣ በጭንቅ ጊዜ ለጭንቅ የተወለደው ጀግናው አባ ኮስትር!» አባ ኮስትር ሲል «ር»ን ጠበቅ እያደረገ «አባ ኮስትር በላይ! ተጎጃም ጀግኖች ጋር ሆኖ፣ ምድረ ባንዳንና የጥልያንን ዘረጠ መውጫ መግቢያ እያሳጣ፣ ጎጃምን የጅግና እናት እንዳላሰኛት ሁሉ እንገሱ ተሸሽት ሲመለሱ፣ አገሩን የሸጠ፣ በወገኑ ያላገጠ ባንዳ ሲሾም ሲሸለም፤ ላገር፣ ለቆሌ ሲል በየበረሃው እየተንከራተተ ለዘውድ ያላበቃ ይመስል አባ ኮስትርን እንደ ወንጀለኛ ባደባባይ ሰቀሉት።»

«ለነገሩማ ጥላውን ሳይቀር የሚጠራጠር ፈሪ ጅግናን ይጠላዋል እንጂ፣ ተገቢውን ክብር መች ሰጥቶት ያውቃል?! ፈሪ መሰሉን ነው የሚያከብር። እና በዚህ በዚህ አድራጎታቸው ሞላውን የጎጃም ጅግና በድለውታል። ይህን በደላቸውን ደሞ ህዝብ አላውቆብኝም ብለው አያስቡም። ድፍን ጎጃም የልቡን በልቡ አርጎ ቀን እየጠበቀ ነው። ለደረሰብን በደል ይቅርታ እንድናደርግ በመጠየቅ ፋንታ፣ ይባስ ብለው፣ እኛ በዳይ፣ እነሱ ተበዳይ መስለው መጡ። ‘ሊበሉዋት ያሰቡዋትን አሞራ ቆቅ ናት ይሉዋታል’ እንደሚባለው፣ እኛው በተበደልን፣ ጎጃም አውራዋን አጥታ ዝም ባለች፤ ቀላድ፣ ብር ታምሳ፣ ቅብጥርጥር የሚሉት ካሳ እንድንከፍላቸው ይዝቱብን ጀመር። መቼም እንገሱ አሞታችንን አንድ ግዜ ጠልቀው ጠጥተውታል። የቀራቸው ቢኖር እኛኑ ጠምደው ማረስ ነው» አለና ለንግግሩ መቁዋጫ ሳይሰጥ ተቀመጠ።

ከተናገረው ሁሉ በተለይ የአባ ኮስትር ስም ሲነሳ «ለዚህ አይነቱ ክፉ ቀን ቢገኝ ኖሮ...» በሚል የጸጸትና የናፍቆት ስሜት ሁሉም በያለበት አባ ኮስትር በላይን ባይነህሊናው እየሳለ በያለበት ይንቆራጠጥ ጀመር።

«ጅግና እስቲ እንደማመጥ!?» አሉ አንድ ሽማግሌ፣ ጢስ የጠጣ ውጅግራቸውን እንደያዙ ከመሀል ብድግ አሉና። ምክራቸውን ለመስማት ይሁን ላባትነታቸው ተገቢውን ክብር ለመስጠት፤ ያ! የሚያጉረመርመው አስፈሪ ድምጽ ከዳር ዳር ረጭ ሲል «ጎበዝ! የዘራነውን እንድንበላ፣ የወለድነውን እንድንስም ያርገን! እግዚአብሄር ጎበዝ አያጥፋ» አሉና ንግግራቸውን በምረቃ ጀመሩ። «ጎበዝ! ይች የምታይዋት ውጅግራ...» አሉ ውጅግራ ጠመንጃቸውን ከፍ አድርገው ይዘው በፍቅር እየተመለከቱዋት። «ይች ውጅግራ በአባ ኮስትር በላይ ግዜ ብዙ ቁም ነገር ሰርታለች፤ አሁንም እንደምትሰራ አልጠራጠርም። እንገሳችን ወዳጅ፣ በተለይ የጅግና ወዳጅ አያውቁም፣ ፈሪን አያርቁም። ይኸ ጠባያቸው መሆኑን አውቀንላቸዋል።»



https://xtremepape.rs/

«ሁላችንም አንገታችንን የደፋን አገዛዙ ተስማምቶን፣ በኑሮዋችን ደልቶን አይደለም፤ ግዜ እየጠበቅን እንጂ! ለሰው ጉልበቱ ግዜ ነው:: እና ጎበዝ! ግዜውን ለኛ ይበለው!» አሉና ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ከፊት ለፊታቸው ከተገተረው ጅባራ ላይ አይናቸውን ተክለው ቀሩ::

ሽማግሌው፣ በጠላት ወረራ ጊዜ፣ ከጀግናው በላይ ዘለቀ ጦር ጋር በመሆን በውድሚት፣ በይናጭ፣ በደብረ ጽሙና፣ በደብረ ወርቅና በአባይ በረሃ በተካሄዱ ጦርነቶች ታላቅ ጀብዱ በመስራት፤ ከበላይ ዘለቀ፣ የፊታውራሪነት ማእርግ ተቀብለዋል:: ከነጻነት መልስ ግን «ሶማ ላይ፣ ከበላይ ዘለቀ ጋር ሆነው በንጉሰነገስቱ ላይ ሸፍተዋል» በሚል ሰበብ ከጠላት በምርኮ ያገኙትን ሀብትና፣ በበላይ ዘለቀ የተሰጣቸውን የፊታውራሪነት ማእርግ ተገፈዋል፣ ተዘርፈዋል::

በላይ ዘለቀ የተያዘ ጊዜ፣ የቀረቻቸው ሃብት ብትኖር የያዙዋት ውጅግራ ብቻ ነበረች:: በላይ ዘለቀ ሲሰቀል፣ እሳቸው ለረጅም ጊዜ ታስረው ተንገላተዋል:: ከስር ከተፈቱ በሁዋላም ከጎጃም እንዳይወጡ ባይነ ቁራኛ እየተጠበቁ የቆዩ፣ ጊዜ አንስቶ ጊዜ የጣላቸው እውቅ አርበኛ ናቸው:: በዚህም ይመስላል ከጊዜ ያገኙትን እውቀት ለመግለጽ «ግዜውን ለኛ ይበለው» ያሉት::

አርበኛው ከጅባራው ላይ አይናቸውን እንደ ተከሉ አንድ መልከ ኈንጉርጉር ወፍ የተገተረውን ደረቅ የጅባራ አካል ጥርስ በመሰለው መንቆርዋ ቦርቡራ ስትገባበትና ስትወጣበት ተመለከቱ:: ይህንንም እንዳንድ ጥሩ ምሳሌ ገመቱት «አያችሁ ይህን ታምር?» አሉ ወደ ተመለከቱዋት ወፍ ጣታቸውን ቀስረው «የወፏዋ መዝጎርጎር ከያውራጃ ግዛቱ የመጣችሁ ልዩ ልዩ ጀግኖች፣ የወፏዋ ብቾኝነት የጎጃም አርበኞች አንድነት፣ ደርቆ በወፏዋ ደካማ መንቆር የተበሳው ጅባራ የእንጉሡ የግዛት ዘመን ማብቂያ ምሳሌ ነው:: የተጨመረው የብር ታምሳ ሳንቲም ግብርና ሊጣል የታሰበው ቀላድም በጀግኖች ተጋድሎ ተረት ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት ጥሩ ምልክ ነው» አሉና ፈገግ አሉ - ባሳብ በፈጠሩት ተስፋ ተደስተው::

አበራ አዳሙ፣ ፍቅር በሲኦል ውስጥ፣ ኢኤምዋይ ማተሚያ ቤት፣ 2008::



https://xtremepape.rs/

**2.**

## **ኵርፊያ**

‘ማርያምን!’ ብያለሁ

በእናትህ ምያለሁ
መለኮት ብትሆንስ
መች እፈራሃለሁ
ተቆይሜሃለሁ!!!

ውሰድብኝ ፅድቁን
    ኩነኔ አከናንበኝ
አሬትም ማር ነበርኩ
    ወትሮም ለሚያነበኝ
እንዲህ እንድናደድ
እንዲህ እንድደፍርህ
ጣቴን እንድቀስር እንድገዳደርህ
አንተ ነህ የገፍከኝ
እና? ምን ልትለኝ?!

አርታኢ ባይኖርህ-ሃያሲ አለሁ እኔ
ደርሰትህ ቅጥአጣ-በዝቶበታል ጠኔ
እንደምን ይዘርፏል -ባባሻ ላይ ቅኔ
ራበኝ! በሚል ቃል -በሚያሙዋሽሽ
ወኔ! ተቀይሜሃለሁ...
አንተ ትፅፋለህ እኛ እናነባለን
ባነበብነው ድርሰት በንባ እንዋጣለን
ትካዝ ይገባናል
ድባቴ ይጫነናል
ሞት አቅፎን ተኝቶ
    ሌት እንዴት ያነጓል!
እዘዝበት እንጂ አንተው ስልጥንበት
ቀለሙም በጅህ ነው፤
    ብራናም ምልቶሃል
ይህን ድርሰት ቅደድ
    መስቀል በዝቶታል
ይሉሃል፤ ይሉሃል
ሁሉም፣ ይከስሃል ይወነጅልሃል

አንተነህ ወጣኙ
አደርጂ ከዋኙ



https://xtremepape.rs/

የተረቶች አባት
ጠርተኸው የቀረ የኖረ ላመታት

አንድም እንደሌለ
ከልብህ ስታውቀው
ሀበሻን ለማስሞት
አንደምን ፈጠንከው?!

'ማርያምን!' ብያለሁ፤ተቀይሜሃለሁ!
ጉምጉምታ አልችልበት
በሆዴ ማብሰልሰል
አንድዶ እየፈጀኝ፤
ፍም ያረግከው ከሰል
'አሜን' አልልህም፤
እያየሁ ከበደል!
'ና! ብላ!' ባይጠፍቶ
አትራሽ አልባሽ ከፍቶ
እህልም እንደሰው

አፈር ቀምሶ በልቶ
ለምንድን ለምንድን
ለምነው ማይበቅል
እህል የሚሞተው

ጠፍቶ የሚያጠፋን
አስታመን ብንለው
ምነው መድሃኔአለም፣ ምነው የማርያም ልጅ
ሰውን ፈጅቶ ማደር፣ ለማን ለምን ሲበጅ?!
"ፍቅር ነኝ" ብለኸን
"ሰላም ነኝ" ብለኸን
እኔን የበላ ሰው ፍፁም አደራብም
ብለህ አጫውተኸን
ለኛው ታርደህልን
ዛሬ ምን ተገኝቶ ፊትህ ጠቆረብን?
ረሃብ መረብ ሆኖህ አንተው አጠመድከን
" ማርያምን!" ብያለሁ፤ ተቀይሜሃለሁ…

**እንዳለጌታ ከበደ፣ "ኩርፍያ"፣ ልብ ሲበርደው፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፣ 2008፡፡**



https://xtremepape.rs/